**ሪቤክ ህግ ቻርተርድ**

**ለቀጥታ ስርጭት**

**በአሜሪካ የሚዲያ መረጃ፣ ዳን ፒተርሰን**

1danpetersen@gmail.com

1-224-489-6900

## ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላን በድጋሚ ላይበር ይችላል።

- ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ አብዛኛዎቹን የቦይንግ 737 ማክስ 8 ክሶችን የሚወክል ሲሆን በኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ 302 ላይ የነበሩ ግብጻዊ መንገደኛን በመወከል በቺካጎ ከተማ ዛሬ ክስ አቅርቧል።
- በቅርቡ ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ እና ግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፕ አንድ የኬንያ ቤተሰብን በመወከል ክስ የመሰረቱ ሲሆን በሁለቱ የቦይንግ 7373 ማክስ 8 አውሮፕላን መከስከስ አደጋዎች ለወከሏቸው ቤተሰቦች አንድ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል።
- የላየን ኤር በረራ 610 ክስ የፍርድ ቤት ሽምግልና ሂደት ለመስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም ተቀጥሯል። ክሱ በዚህ ካልተቋጨ ሁለቱ የቦይንግ አውፕላን አደጋ ክሶች ተጣምረው የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል ግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፕ ለፍርድ ቤቱ ያመለክታል።

**ቺካጎ - ነሃሴ 23 ቀን 2011 ዓ.ም.**

አብዛኛዎቹን የቦይንግ 737 ማክስ 8 አደጋ ተጎጂ ቤተሰቦችን የሚወክለው ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ እና ግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፕ አንድ ግብፃዊ መንገደኛ ቤተሰብን በመወከል ዛሬ ቺካጎ በሚገኘው የአሜሪካ ፍርድ ቤት ክስ መስርተዋል።

በቦይንግ 737 ማክስ 8 ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የቀጠሉ ሲሆን የኢንዱስትሪው ውስጥ አዋቂዎች አውሮፕላኑ በድጋሚ የሚበር መሆኑን በመጠራጠር ላይ ናቸው። ህምሌ 17 ቀን 2011 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የ2019 ሁለተኛው ሩብ ዓመት ገቢ ቦይንግ ሲያሳውቅ የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ ዴኒስ ሙይለንበርግ የአውሮፕላኑ ዓለምዐቀፍ ክልከላ ከቀጠለ አውሮፕላኑን ማመረት ሊያቋርጥ እንደሚችል ገልጸዋል። በተጨማሪም እነዚህ አውሮፕላኖች በቅርቡ ወደአገልግሎት ካልተመለሱ በሬንተን ዋሽንግተን (አሜሪካ) በሚገኘው የቦይንግ ፋብሪካ 12000 ሰራተኞች ስጋት ላይ ይወድቃሉ።

ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ እስካሁን በሁለቱ የቦይንግ 737 ማክስ 8 አደጋዎች የተነሳ በቦይንግ ኩባንያ ላይ 44 ክሶች ቺካጎ በሚገኘው የአሜሪካ ፌደራል ፍርድ ቤት መስርቷል። ተቋሙን በመወከል ማኑዌል ቮን ሪቤክ ሲናገሩ <<ዛሬ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ 302 አደጋ የሞቱ የግብፅ መንገደኛ ስም የክስ መዝገብ ከፍተናል። ደንበኞቻችን ለደረሰባቸው ጉዳት በአጠቃላይ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ እንዲከፈላቸው ጠይቀናል። ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ እና ግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፕ በሁለቱ አደጋዎች የተጎዱ 67 ቤተሰቦችን፣ አብዛኛዎቹን መንገደኞች እና የበረራ አስተናጋጆች የሚወክል ሲሆን ከዚህ በኋላም ለደንበኞቻችን ፍትህን በመሻ ት ተጨማሪ ክሶችን በአሜሪካ ፍርድ ቤቶች እንመሰርታለን>> ብለዋል።

ይህ ክስ ወንድ ልጃቸውን በአሳዛኙ የአየር መንገድ በረራ 302 በአጡ እናት የቀረበ ሲሆን የ737 ማክስ 8 አምራች ቦይንግ ላይ በብዛት እየተከፈቱ ከሚገኙ ክሶች መካከል አንዱ ነው። በአደጋው ስድስቱ ተጎጂዎች ግብፃውያን ሲሆኑ ሁሉም የአገሪቷ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረቦች ነበሩ።

ልጃቸውን በተመለከተ ሲገልጹ <<ልጄን መልካም መንገድ እንዲሆንለት ስነግረው ለመጨረሻ ጊዜ እንደማየውና እንደማናግረው ጨርሶ አላሰብኩም ነበር>> ብለዋል። <<የመጀመሪያ ወንድ ልጄን በዚህ አደጋ በማጣቴ እጅግ ተጎድቻለሁ። አደጋው ከደረሰ በኋላ ባሉት ወራት ቦይንግ በአውሮፕላኑ ሶፍት ዌር ላይ ችግር ሊኖር እንደሚቸል እያወቀ አውሮፕላኖቹ መብረር እንዲቀጥሉ ማድረጉ አሳፋሪ ነው።>> በመቀጠልም ሲናገሩ <<ለእኔ የሚመስለኝ ቦይንግ የድርጅቱን ትርፍ ከመንገደኞች ሕይወት የሚያስቀድም መሆኑን ነው።>> <<በአውሮፕላኖቹ ላይ የሚቀርቡ ዜናዎች እንዲሁም የመጀመሪያው አደጋ ከደረሰ አንድ ዓመት እየተቃረበ ቢሆንም አውሮፕላኖች መብረር አለመጀመራቸው ከፍተኛ እክል (ችግር) እንዳለ ያሳያል።>> የመንገደኛው ወንድም ዶክተር መሃመድ በበኩላቸው <<ወንድሜ በአደጋው ከሞተ በኋላ ቤተሰባችን ውስጥ መሸከም የማንችለው ጉዳት ደርሶብናል። ሁሉን ነገር ሕይወቴን ጨምሮ እንዳጣሁ ይሰማኛል፤ ህልማችንን አጥተናል፤ የቤተሰባችን መሪ ነበር። ለዚህ አደገኛ ድርጊት ኃላፊነት ያለባቸው በሙሉ እንዲቀጡ እንፈልጋለን>> ብለዋል።

አሁን የደረሰንበት ሁኔታ ብዙ ሺህ የ737 ማክስ ትዕዛዞች በተቀበለው ቦይንግ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ነው። የሁለቱ 7373 ማክስ አውሮፕላኖች አደጋ ዋና መነሻዎች ተመሳሳይ ቢመስሉም አደጋዎቹ አሁንም በምርመራ ላይ ናቸው። የኢንዶኔዥያ እና ኢትዮጵያ መርማሪዎች የተበላሹ መለኪያዎች (sensors) እና የአውሮፕላኑን አፍንጫ በበረራ ወቅት ወደታች የሚመልስ የበረራ መቆጣጠሪያ ስርዓት ላይ ትኩረት አድርገዋል። በመጋቢት ወር የኢትዮጵያ ትራንስፖርት ሚኒስትር ሁለቱ አደጋዎች <<ግልጽ የሆነ ተመሳሳይነት>> እንዳላቸው አስተያየት ሰጥተዋል። በተጨማሪም የሳተላይት መረጃዎች የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ 302 የመጨረሻ የበረራ መስመር ጥቅምት 19 ቀን 2011 ዓ.ም. ከተከሰከሰው የላየን

ኤር በረራ ጋር እጅግ ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታሉ። የአውሮፕላኑን አፍንጫ ወደላይ እና ወደታች የሚያንቀሳቅሰው ሆሪዞንታል ስታቢላይዘር (horizontal stabilizer) አካል የሚያንቀሳቅሱ ብሎኖች አውሮፕላኖቹን ወደታች እንዲያዘቅዝቁ በሚያደርግ ቦታ ላይ እንደነበሩ አስተውለዋል።

የሪቤክ ሕግ ቻርተርድ ወ/ሮ ሞኒካ ኬሊ <<ከላየን ኤር 737 ማክስ 8 አደጋ በኋላ ቦይንግ ተመሳሳይ አደጋ እንዳይከሰት በፓይለቶች መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ያሳወቀ ቢሆንም እነዚህ መመሪያዎች በፍጹም በቂ ያልነበሩ ሲሆን ሁለተኛው አደጋ እንዳይፈጠር ማስቆም አልቻሉም ብለዋል። አደጋ መርማሪዎች የኢትዮጵያ አየር መንገዱ አብራሪዎች ሙሉ በሙሉ የተሰጣቸውን መመሪያ መፈጸማቸውን እንዲሁም በተደጋጋሚ አውሮፕላኑን ለማረጋጋት መሞከራቸውን እና በራሱ ከሚሰራው የሞተር መጥፋት መከላከያ ሥርዓት አውሮፕላኑን በማላቀቅ ለመቆጣጠር በተደጋጋሚ ሞክረዋል>>። ሞኒካ ኬሊ አክለውም <<ይህ ትክክለኛ የስግብግብነት ማሳያ ነው፤ ምክንያቱም ቦይንግ ለመንገደኞቹ ምንም ሳያስብ በረራዎች እንዲቀጥሉ አድርጓል>> ብለዋል። በመጨረሻም ወ/ሮ ኬሊ <<የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራን የሚመለከተው ክስ መስከረም 7 ቀን እንዲሁም የላየን ኤር በረራ ክስ ጥቅምት 7 ቀን የፍርድ ሂደታቸው ይታያል>> ብለዋል።

የግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፑ ዲኦን ቦታ << በፍርድ ቤት በቅርብ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፕ የላየን ኤር እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ክሶች በተለያዩ ዳኞች የሚጋጩ ትዕዛዞች እንዳይሰጡባቸው ለማድረግ ሁለቱ ክሶች ተጣምረው እንዲታዩ የሚያመለክት ሲሆን ከሪቤክ ሕግ ቻርተርድ ጋር በመሆን ጉዳዮቹ በግልጽ የክስ ሂደት እንዲታዩ ያደርጋል>>።

ሚ/ር ዲኦን ቦታ በተጨማሪም << የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ 302 ደንበኞቻችን ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላኖች የመጀመሪያው አደጋ ሲደርስ ለምን እንዳይበሩ እንዳልተደረገ ማወቅ ይፈልጋሉ? የአሜሪካ ፌደራል አቪዬሽን ባለሥልጣን ምን ሚና ነበረው? ባለሥልጣኑ የቦይንግ ድርጅትን ወንጀላዊ ድረጊቶች እየደበቀ ነበር? ቦይንግ አውሮፕላኖች ዕክል እንዳለባቸው እያወቀ ነገር ግን በሁለተኛው አደጋ ተጨማሪ 157 ሰዎች ከመሞታቸው በፊት አውሮፕላኖቹ እንዳይበሩ አላደረገም። የቦይንግ ወንጀል ድርጊቶች ሊቀጡ ይገባል። የምንወክላቸው ቤተሰቦች እውነታው እስኪታወቅ እና ለድርጊቱ ተጠያቂ የሆኑ በፍርድ ቤት እስኪቀጡ ድረስ የሕግ ቢሯችንና ወደኋላ እንዳይል ጠይቀውናል።

በናይሮቢ የግሎባል አቪዬሽን ግሩፕ ወኪል የሆኑት ጠበቃ ዴቪድ ንጆሮጌ <<ቦይንግ የመጀመሪያው አደጋ ከደረሰ በኋላ 737 ማክስ 8 አውሮፕላኖች እንዳይበሩ አለማድረጉ ወንጀል ነው፤ ነፍስ ግድያ ነው። በኬንያ፣ በኢትዮጵያና ሌሎች ዜጎቻቸውን ያጡ አገራት በቦይንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የሥራ አመራር ቦርድ እና ሌሎች በድርጅቱ ውሳኔ አሰጣጥ የተሳተፉ አካላት ላይ የወንጅ ክስ እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን። የቦይንግ ኩባንያ ድርጊት አስጸያፊ እና ወንጀል ነው>> ብለዋል።

ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ በ48 የአውሮፕላን አደጋዎች ከ74 አገራት የመጡ ተጎጂዎችን ወክሏል። ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ በዓለም አብዛኛዎቹን የአውሮፕላን አደጋ ተጎጂዎች ይወክላል።

ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ በዋነኛነት በአውሮፕላን አደጋዎችና ሌሎች ከፍተኛ ጥፋቶች ጋር በተገናኙ ክርክሮች ዙሪያ የሚሰራ ሲሆን ዋና ጽህፈት ቤቱ ቺካጎ ሲሆን በለንደን፣ ሻንጋይ፣ ሮም፣ ጃካርታ፣ ኢስታንቡል፣ እና ሊማ ተባባሪዎች አሉት። ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ በላየን ኤር በረራ 610 እና ኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ 302 አደጋዎች ተጎጂዎች ውስጥ ከ66 በላይ ቤተሰቦችን የሚወክል ሲሆን ይህም ቁጥር ከየትኛውም የሕግ ቢሮ የበለጠ ቁጥር ነው።

ግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፕ በአሜሪካ፣ አውሮፓ፣ አፍሪካና እስያ በ40 አገራት ቢሮ ያሏቸው የአሜሪካና ዓለምዐቀፍ ሕግ ቢሮዎችና ጠበቆች ሽርክና ነው። ግሎባል አቪዬሽን ሕግ ግሩፕ እና ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ 302 ክሶችን በጋራ ይከራከራሉ።

በአሁኑ ወቅት ሪቤክ ሕግ ቻርተርድ ከአሜሪካ፣ አውሮፓ፣ አፍሪካ፣ እስያና ፓሲፊክ ውቅያኖስ አካባቢ የመጡ ደንበኞችን በመወከል በሰሜን አሜሪካ፣ እስያ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ ማዕከላዊ አሜሪካ፣ ካሪቢያን፣ አውሮፓ እና አፍሪካ ባጋጠሙ የአውሮፕላን ክስተቶች ተጎጂዎችን በመወከል በአሜሪካ ፍርድ ቤቶች ክርክር ላይ ይገኛል። የሪቤክ ሕግ ቻርተርድ ስኬት ለተጎጂ ቤተሰቦች ባስገኘው ከፍተኛ የካሳ ክፍያ እና በዓለምአቀፍ የአቪዬሽን ደህንነት መሻሻሎች ይታያል።